
# የተፈሪ፡ መኰንን፡ ትምህርት፡ ቤት፡
# አጭር፡ ታሪክ።

# SHORT HISTORY OF TAFARI MAKONNEN SCHOOL.



*We are the boys of Tafari Makonnen!*

ተኀትመ፡ ዝንቱ፡ መጽሐፍ፡ በ፳ ወ፩ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ፡ ለቀዳማዊ፡
ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ።

በብርሃንና ፡ ሰላም፡ ማተሚያ፡ ቤት፡ ታተመ ።

## ማ ው ጫ ።


ገጽ ፡

፩ ፤ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡
ሲከበር ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡
ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ። . . . . . . ፩
፪ ፤ የተፈሪ፡መኰንን፡ተማሪ፡ቤት፡አጭር፡ታሪክ፡ከ፲፱፻፲፯፡እስከ፡፲፱፻፶፪ዓ.ም. ፫
፫ ፤ ተፈሪ፡መኰንን፡ተማሪ፡ቤት፡መጀመሪያ፡ሲከፈት፡ልዑል፡የኢትዮጵያ፡
መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ። ፳፱
የተማሪ፡ቤቱ፡ሹም፡ሐኪም፡ወርቅነህ፡በዚያው፡ቀን፡የተናገሩት፡ቃል ። ፴፫
፬ ፤ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፤ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡
ከልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የተሰጠው ። . . . . ፵፯
፭ ፤ ለተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እርዳታ ፡ የሰጡ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ፶፩
፮ ፤ የተማሪዎች ፡ ስም ፡ ከ፲፱፻፲፯ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም. . . ፶፪
፯ ፤ የተማሪዎች ፡ ስም ፡ ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ም. እስከ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. . ፶፱
፰ ፤ የትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ም / ሚኒስትር ፡ የክቡር ፡ አቶ ፡ አካለ ፡
ወርቅ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡ ንግግር ፡ ፷፫

ሰች ፡ መሠረት ፡ እንጂ ፡ በአንዳንድ ፡ ትውልድ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ በሚሠራው ፡ አለ መሆኑን ፡ ተረድተን ፡ እነዚህም ፡ ቅርሶች ፡ ብዙ ፡ መሥዋዕትነት ፡ የሚጠይቁ ፡ መሆናቸውን ፡ አውቀን ፡ በየዘመኑ ፡ የሚደርሱትን ፡ ችግሮች ፡ ለማስወገድ ፡ ለሚ መጣውም ፡ ትውልድ ፡ አለስልሰንለት ፡ ለመሄድ ፡ ብዙ ፡ ትግል ፡ አደረግን ። ፈተ ናዎችንም ፡ በሃይማኖት ፡ ለማለፍ ፡ ቻልን ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ባቆምነው ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሊገኝ ፡ ከሚቻለው ፡ ትም ህርት ፡ ሌላ ፡ ለመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ትምህርት ፡ ለማዳረስ ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ለማስፋፋት ፡ ምኞታችን ፡ ስለነበረ ፤ በተለየ ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በማኅበር ፡ ስም ፡ ትምህርትን ፡ ለኢትዮጵያውያኖች ፡ ለሚሰብክና ፡ የትምህርት ፡ ቤትም ፡ ለማቆም ፡ ለሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ ላንዳቸውም ፡ እርዳታ ፡ ያላደረግንለት ፡ አይገኝም ።

ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ በትምህርት ፡ አእምሮአቸውን ፡ ከጐለመሱ ፡ በኋላ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ ፡ አገራቸውን ፡ የሚረዱ ፡ እንዲዘጋጁ ፡ ከማድረግ ፡ በቀር ፤ ላገር ፡ መጠበቂያ ፡ ከሚሆኑት ፡ ጥበቦች ፡ ወገን ፡ እንደጦር ፡ ሠራዊት ፤ ፖሊስ ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለማቋቋምና ፤ በጠቅላላውም ፡ የሕዝብ ፡ ትም ህርት ፡ አጠገብ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንዲሄድ ፡ አከታትለንለት ፡ ነበር ።

ምንም ፡ ሥራና ፡ ጊዜ ፡ ለሰው ፡ አቅም ፡ መጠንና ፡ ልክ ፡ ቢኖራቸው ፡ በእምነት ፡ በትዕግሥት ፤ በጥንካሬና ፡ በረጅሙ ፡ አስቦ ፡ በመሥራት ፡ ዋና ፡ ዋና ውን ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ለማጠቃለል ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ በማመን ፡ ዋናው ፡ ጥረ ታችንና ፡ ድካማችን ፡ ለሚመጣው ፡ ትውልድ ፤ ያለፉ ፡ ዘመኖች ፡ የሥራ ፡ ውዝፍ ፡ ሳይቆየው ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ አዲስ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተወርውሮ ፡ ተመዛዛኝ ፡ ኑሮውን ፡ እንዲከተል ፡ ነበር ።


ይህንም ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮውን ፡ ለሕዝባችን ፡ ስናደራጅ ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በመግባትና ፡ የኬሎግን ፡ ውል ፡ በመፈረም ፡ ለጊዜው ፡ የተገኘውን ፡ ሰላማዊ ፡ የእንተርናሲዮናል ፡ ዋስትና ፡ ገዝተንለት ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ እንድ ትደርስ ፡ ለምንደክምበት ፡ ሰላማዊ ፡ ሥራችን ፡ የሚያሰናክል ፡ ጠላት ፡ ተነሥቶ ፡ አገራችንን ፡ በመውረር ፡ የደከምንበትን ፡ ሁሉ ፡ አፈረሰው ። በየዘመኑ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እንቅፋቶች ፡ እየገጠሙ ፡ ሥራችን ፡ ባይሰናከል ፡ ኖሮ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ሥልጣኔዋን ፡ ከአዲሱ ፡ የዓለም ፡ ጥበባዊ ፡ እርምጃ ፡ ጋር ፡ እንድታስተባብር ፡ ጀምረናቸው ፡ የነበሩ ፡ ሥራዎች ፡ ፍሬ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ አስቀድሞ ፡ ይታይ ፡

## ተ ፈ ሪ ፡ መ ኰ ን ን ፡ ተ ማ ሪ ፡ ቤ ት ፡

### ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ. ም.

በኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የሥልጣኔ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማቋቋም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ የተረዱት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ( በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ ልዑል ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ሲባሉ ፡ ሳሉ ፡) በልዩ ፡ ገንዘባቸው ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡



የመጀመሪያው ፡ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡


በዘመናዊ ፡ አሠራር ፡ አሰናዱ ። ትምህርት ፡ ቤቱም ፡ « ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡» ተብሎ ፡ በስማቸው ፡ ተጠራ ። ይህ ፡ ሕንፃ ፡ ከ $ 300.000 በላይ ፡ ተከፍሎበታል።

* * *

### ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ. ም.

በዚህ ፡ ዓመት ፡ ስለአዳሪዎች ፡ ተማሪዎች ፡ ለመኝታ ፡ የሚሆን ፡ ባለ ፡ ሦስት ፡ ፎቅ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ተሠራ ። ( ሥዕሉን ፡ በ፭ኛው ፡ ገጽ ፡ ተመልከት ፡)

ለዚህ ፡ ሕንፃ ፡ $130.000 ተከፍሎበታል ። ዳግመኛ ፡ ለተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ግቢ ፡ ፳፫ ፡ ኤክታር ፡ መሬት ፡ ተከልሎ ፡ ዙሪያው ፡ አጥሩ ፡ በደንጊያ ፡ ካብ ፡ ታጠረ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ አውሮፓን ፡ ለማየት ፡ ሚያ



The Dormitory Building Erected in 1925.

በ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. የቆመው መኝታ ቤት ።

የተማሪዎችን ፡ ቍጥር ፡ እስከ ፡ 850 ለማድረስ ፡ አራት ፡ አዳዲስ ፡ የትምህርት ፡ መስጫ ፡ ክፍሎች ፡ ተሠሩ ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ የከተማ ፡ ሕዝብ ፡ የሚኖርባቸው ፡ ፲፩ ፡ የሚሆኑ ፡ ቤቶች ፡ ላዳሪዎች ፡ የሚሆኑ ፡ መኝታ ፡ ቤቶች ፡ ለማዘጋጀት ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ እንዲደረቡ ፡ ተደረገ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ያዳሪዎች ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ከ125 ወደ ፡ 440 ወጣ ። ዘጠኝ ፤ ሕመምተኞች ፡ የሚያስተኛ ፡ አዲስ ፡ የሕክምና ፡ ክፍል ፡ ተቋቋሞአል ። ለ440 አዳሪዎች ፡ የሚበቃ ፡ የመብል ፡ ቤት ፡ አዳራሽና ፡ 200 ወንበር ፡ ያለበት ፡ የቴአትር ፡ አዳራሽ ፡ ተሠርቶአል ።

ለቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚሆን ፡ ክፍልና ፡ ሁለት ፡ ላቦራቶሪዎች ፡ ተደራጅተዋል ። በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሰፊ ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ መንገዶች ፡ ተሠርተው ፡ የኤሌክትሪኩ ፡ ብርሃን ፡ ተቀጥሎአል ።

ለዚህ ፡ ሥራ ፡ እስከ ፡ 300.000 ብር ፡ የሚገመት ፡ ወጭ ፡ ተደርጎበታል ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ በላይ ፡ አራት ፡ የጨዋታ ፡ ሜዳዎች ፡ ተደልድለዋል ።

በነሐሴ ፡ ወር ፡ መከከል ፡ የታደሰውን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ የሚያከሒዱ ፡ አራት ፡ ከናዳውያን ፡ ከአሜሪካ ፡ መጡ ፤ አምስተኛው ፡ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ እንዲከተላቸው ፡ ተደረገ ።

አዲሶቹ ፡ መምህራን ፡ ሥራቸውን ፡ ጀመሩ ። ከታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ጀምረው ፡ አዲስ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ በማዘጋጀት ፤ ትምህርቱ ፡ ጥዋትና ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ እንዲሰጥና ፡ ከትምህርት ፡ በኋላ ፡ ጥዋትና ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ የትምህርት ፡ ማጥኛ ፡ ጊዜ ፡ ተወሰነ ። ከራት ፡ በኋላ ፡ ከ፩ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ እስከ ፡ ፪ ፡ ሰዓት ፡ ከ፴ ፡ ደቂቃ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኞች ፡ ተማሪዎች ፡ ትምህርት ፡ የሚያጠኑበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰነ ።

በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ አዲሱ ፡ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ ዶክቶር ፡ ማት ፡ በተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያ፩ኛና ፡ የ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ክፍሎች ፡ በማቋቋም ፡ አስፈላጊዎችን ፡ የትምህርት ፡ መሣሪያዎች ፡ ለመግዛት ፡ ወደ ፡ አሜሪከና ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ እንዲሔዱ ፡ የትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ላካቸው ። ዶክቶር ፡ ማት ፡ ባልነበሩበትም ፡ ጊዜ ፡ ምስተር ፡ ሌግ ፡ ዚፌል ፡ ተቀብለው ፡ ሲያካሒዱ ፡ ቆዩ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከፍጻሜ ፡ ደርሶ ፡ ስለነበረ ፡ የሳይንስ ፡ መሣሪያዎች ፤ የትምህርትና ፡ የንባብ ፡ መጻሕፍት ፤ የሲኒማ ፡ መሣሪያዎች ፡ ( ፕሮጀክተር ፡ ) ፊልም ፡ የሚታይባቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ( ላንቴርን ፡ ሳላይድ ፡ ) የፊልም ፡ ጥቅሎችና ፡ እነዚህን ፡ የመሰሰሉ ፡ ለትምህርት ፡ ቤት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ መሣሪያዎች ፡ ለማግኘት ፡ ተቻለ ።

የስፖርት ፡ ጨዋታ ፡ ወድያውኑ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ብዙዎች ፡ የግር ፡ ኳስ ፡ ተጨዋቾች ፡ ጓዶች ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ተቋቋሙ ።


## ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ. ም.

በ፲፱፻፴፱ ዓ. ም. ፡ መጀመሪያ ፡ ከአሜሪካና ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ከተገዙት ፡ የትምህርት ፡ መሣሪያዎች ፡ ጥቂቶቹ ፡ ደርሰው ፡ ተማሪዎቹ ፡ እንዲጠቀሙባቸው ፡ ሥራ ፡ ይሠራባቸው ፡ ጀመር ።

የካናዳውያን ፡ መምህራን ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ ሆኖ ፡ በ፪ኛው ፡ ደረጃ ፡ ክፍል ፡ አምሳ ፡ ተማሪዎች ፡ ነበሩ ።

በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ 450 አዳሪ፡ ተማሪዎች ፡ የሚችል ፡ የመብል ፡ ቤት ፡ አዳራሽ ፡ የትምህርት ፡ ማጥኛ ፡ አዳራሽና ፡ አምስት ፡ የመኝታ ፡ ክፍሎች ፡ የሚገኙበት ፡ ሕንፃ ፡ መሠረቱ ፡ ተጣለ ።

ይህ ፡ ዓመት ፡ እንዲሁ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚደራጅበት ፡ ዘመን ፡ ነበር ። የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መሣሪያዎች ፡ በየጊዜው ፡ ስለደረሱ ፡ ተማሪዎች ፡ ወዲያውኑ ፡ በመሣሪያዎቹ ፡ እንዲሠሩባቸው ፡ ተደረገ ።



የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ት· ቤ· የአናጢነት ፡ ክፍል ።

*Woodwork Shop.*




የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ተማሪዎች ፡ በአናጢነት ፡ ክፍል ፡ ሲሠሩ ።
*Elementary Pupils Working in the Woodwork Shop.*

## ፲፱፻፵ ፡ ዓ. ም.

ይህ ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በሰፊው ፡ የተስፋፋበት ፡ ዘመን ፡ ነው ። በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ፳፫ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ ሲገኙበት ፤ ካንድ ፡ ፈረንሳዊና ፡ ካንድ ፡ ህንዳዊ ፡ በላይ ፡ በሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ፳፩ ፡ ካናዳውያን ፡ መምህራን ፡ ይገኛሉ ።

በ፪ኛው ፡ ደረጃ ፡ ክፍል ፡ ፩፻፳ ፡ ተማሪዎች ፡ ይገኛሉ ። የፊዚክ ፤ የኬሚያና ፡ የባዮሎጂ ፡ ላቦራቶሪዎች ፡ በሚገባ ፡ ተሰናድተዋል ። መሣሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ ለሳይንስ ፡ ትምህርት ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ተደርጎ ፡ ከዚህም ፡ በላይ፡ ኛው ደረጃ ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ በ፲ ፡ ቀን ፡ በ፲ ፡ ቀን ፡ በፊዚክ ፡ በኬሚያና ፡ በባዮሎጂ ፡ ላቦራቶሪዎች ፡ ሙከራ ፡ እንዲያደርጉባቸው ፡ ሥራው ፡ ተጀምሮአል ።

የስፖርት ፡ ጨዋታ ፡ በዱስ ፡ መንፈስ ፡ እንዲካሄድ ፡ ተደርጓል ። የግር ፡ ኳስ ፡ የቮልቦልና ፡ የባስኬትቦል ፡ ጨዋታ ፡ እሽቅድድም ፤ ከፍታ ፡ ዝላይና ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ጨዋታ ፡ በሚያስገርም ፡ አኳኋን ፡ ተካሂዶአል ። ዓሥር ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ ማኅበሮችና ፡ ስምንት ፡ ጓዶች ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ።





ኤሌክትሮ ፡ ማግኔቲዝም ፡ ምርመራ ፡

*Secondary Pupils at Work in The Chemistry Laboratory.*


የ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ተማሪዎች ፡ በሳይንስ ፡ ጥናት ፡ ክፍል ፡

*Experimenting in Electromagnetism.*






የፊዚክስ ፡ ክፍል ፡ *Physics Laboratory.*




ለጂምናስቲክ ፡ ሥራ ፡ ጊዜ ፡ *An Athlete at work.*

በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የተማሪዎች ፡ የጅ ፡ ሥራ ፡ ክፍል ፡ ተመርቆ አል ። በከፍተኞች ፡ ክፍሎች ፡ የሚገኙት ፡ ተማሪዎች ፡ በክፍል ፡ ተከፋፍለው ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ ከ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ የጨዋታውን ፡ ሜዳ ፡ በመደልደል ፡ በተራ ፡ ይሠራሉ ። ይህን ፡ የመሰለው ፡ አስደሳች ፡ ሥራ ፡ ለተማሪዎች ፡ ከትምህርቱ ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጣቸዋል ።



የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ትእይንት ፡

*Physical Training Exhibition.*



ተማሪዎች ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍት ፡
Library and Reading Room.

የኮንፌራንስ ፡ ንግግር ፡ ማኅበሮች ፡ በእንግሊዛውያን ፡ መምህራን ፡ ተጠባባቂነት ፡ ተቋቁሞ ፡ ሥራውን ፡ አላቋረጠም ።

ተማሪዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቴያትር ፡ ጨዋታ ፡ እያዘጋጁ ፡ እያንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ በቴያትር ፡ ጨዋታ ፡ ያለውን ፡ ስጦታ ፡ ያሳያል ።


በኅዳር ፡ ወር ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ያናጢ ፡ ሥራ ፡ ክፍል ፡ ተቋቁሞአል ። በዚሁም ፡ ክፍል ፡ ለእንጨት ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ መኪናዎችና ፡ 36 ፡ ያናጢ ፡ ጠረጴዛዎች ፡ ስለተገኙ ፡ እያንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ፳ ፡ በሚያህሉ ፡ መሣሪያዎች ፡ ይሠራባቸዋል ። በየሳምንቱ ፡ 228 ፡ ተማሪዎች ፡ ችሎታ ፡ ባለው ፡ መምህር ፡ ተጠባባቂነት ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ይሠራሉ ።

በክረምቱ ፡ የዕረፍት ፡ ወራት ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የቀሩት ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ተማሪዎች ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምሳሌ ፡ የአላፊነትን ፡ ሁናቴ ፡ ለመልመድ ፡ የሚያገለግል ፡ ጥናት ፡ አቋቁመው ፡ ነበር ። የትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በዕረፍቱ ፡ ወራት ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ የሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ የመጫወቻ ፡ ሜዳዎችን ፡ ጽዳት ፡ የማስታወቂያ ፡ ሚኒስቴር ፡ በየዕለቱ ፡ የሚወጣውን ፡ ጋዜጣ ፡ እየ

ተጠባበቁ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴርና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሌሎች ፡ ሚኒስቴሮችም ፡ ነበሩ ። ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ዘዴ ፡ በከፍተኞች ፡ ተማሪዎች ፡ የአላፊነትን ፡ የድርጅትንና ፡ የሙከራን ፡ መንፈስ ፡ ያስፋፋል ።

## ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.

በዚህ ፡ ዓመት ፡ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተመሠረተበትን ፡ ፳፭ኛውን ፡ ዓመት ፡ ያከብራል ። በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ፳፫ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡




አዲሱ ፡ የመኝታ ፡ ቤት ፡ ሕንፃ ፡ ሲሠራ ፡

*The New Dormitory Building under Construction.*

፳፯ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መምህራን ፡ ይገኙበታል ። የ፩ኛ ፡ ደረጃ ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ 210 ፡ ሲሆኑ ፡ ባንደኛው ፡ ደረጃ ፡ ክፍል ፡ 900 ፡ ይሆናሉ ።


ባለፈው ፡ ጥር ፡ ወር ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ታሪክ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜውን 30 ፡ ተማሪዎች ፡ ወደ ፡ ለንዶን ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ ለመግባት ፡ በማትሪኩሌሽን ፡ ፈተና ፡ ቀረቡ ።

ዕቃው ፡ በሙሉ ፡ የተዘጋጀለት ፡ ለአንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ በሚቃረብ ፡ ገንዘብ ፡ የተሠራው ፡ ያዲሱ ፡ ሕንፃ ፡ ሥራ ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ስለተፈጸመ ፡ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተመሠረተበትን ፡ ፳፭ኛውን ፡ ዓመት ፡ በሚያከብርበት ፡ ቀን ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይመረቃል ።



አዲሱ ፡ ሕንፃ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ቀርቦ ፡ ይታያል ፡ ፲፱ ፻፵፪ ፡ ዓ. ም. ሚያዝያ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ተከፈተ ።

*The New Dormitory Building Nearing Completion (Officially opened 27th April 1950).*



ባዲሱ ፡ ሕንፃ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ከ፮ቱ ፡ መኝታ ፡ ቤቶች ፡ አንዱ ፡

*One of the Six Dormitories in the New Dormitory Building.*



ሚያዝያ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ልዑል ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ተማሪ ፡ ቤቱን ፡ ሲከፍቱ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

የተወሰነ ፡ ቦታ ፡ የሌለህ ፡ በሁሉ ፡ የመላህ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፤ በፈቃድህ ፡ ያስገርመርኸኝን ፡ ያስፈጸምከኝ ፡ ይህንንም ፡ እንድናገር ፡ የፈቀድህልኝ ፡ ምስጋና ፡ ላንተ ፡ ይሁን ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታላቅነትና ፡ ቀደምትነት ፤ ይልቁንም ፡ በአረመኔ ፡ ተከባ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቷና ፡ ስለ ፡ ነፃነቷ ፡ እየተጋደለች ፡ የቆየች ፡ መሆኗን ፤ እንኳን ፡ እኛ ፡ ገንዘባችን ፡ ገንዘቧና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ያገሯን ፡

መልካምነት ፤ የታሪኳን ፡ ታላቅነት ፤ በመጽሐፍም ፤ በቃልም ፡ ሲናገሩት ፡ የምን ሰማው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሆነች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነበር ፡ ምን ፡ ይጠቅማታል ።

በመንግሥታቸው ፡ ጽናት ፤ ባናኑርዋቸው ፡ ሥርዓት ፡ ፍጹም ፡ ተስፋ ፡ እንዳላቸው ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፤ በአፍሪቃ ፡ ነፃነቷን ፡ ይዛ ፡ ለቆየችው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የምትደረጅበት ፤ ለመንግሥቷ ፡ ጽናት ፤ ለሕዝቧ ፡ ድሎት ፡ የሚሆናት ፡ ዕውቀትን ፡ ፈልጎ ፡ አግኝቶ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ነው ። ሥራም ፡ ለመሥራት ፣ አስቀድሞ ፡ መሣሪያን ፡ ማበጀት ፡ ነው ።

ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነትና ፡ ጽናት ፡ ወሰኗን ፡ ጠብቆ ፡ አሳፍሮ ፤ አስከብሮ ፡ ለማኰራትና ፡ የሕዝቧ ፡ ልብ ፡ የታመነ ፡ ኃይል ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ፤ መሣሪያው ፡ ትምህርት ፡ መማር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ሕዝባቸው ፡ በዕውቀት ፡ እንዲሠለጥን ፡ ዳግማዊ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ እንዳቆሙ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቀው ፡ ነው ። ለመማርም ፡ ትጋትና ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ያስፈልጋል ።

ተማሪ ፡ ቤት ፡ ለማቆምና ፡ ልጆቻቸው ፡ ያልሆኑ ፡ ተማሪዎችን ፡ መርዳት ፤ ልጆቻቸውንም ፡ እንዲማሩ ፡ ማድረግ ፤ ኢትዮጵያን ፡ ለሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሲጠይቁት ፡ አገሬን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እወዳለሁ ፡ የማይል ፡ ሰው ፡ የለም ። ይህ ፡ እስካሁን ፡ ያፍ ፡ ልማድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወዳጅ ፡ የሚሉትን ፡ ሰው ፡ በችግሩ ፡ ካልረዱት ፡ በተጨነቀ ፡ ጊዜ ፡ ካልደረሱለት ፡ የወዳጅነቱ ፡ ምልክት ፡ እምን ፡ ላይ ፡ ነው ።

አሁንም ፡ ለሀገሬ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወዳጅ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የወዳጅነቱን ፡ ምልክት ለማሳየት ፤ ለተማሪ ፡ ቤት ፡ መርዳትና ፡ የሚቻለውም ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ በመሥራት ፡ ልጅን ፡ ማስተማር ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህንም ፡ የሚያደርጉ ፡ ሁሉ ፡ የውነት ፡ የሀገራቸውን ፡ ፍቅር ፡ ገለጹ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የልጆቹንና ፡ የወገኑን ፡ መማር ፡ የሚወድና ፡ ለተማሪ ፡ ቤትም ፡ የሚረዳ ፡ ሰው ፡ መጀመሪያ ፡ ራሱ ፡ ይጠቀምበታል ፤ ሁለተኛው ፡ በልጁ ፡ በወገኑ ፡ ጥፋት ፡ ሳይጸጸት ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይኖራል ። ሶስተኛም ፡ ለሀገሩ ፡ የውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ እንዳለው ፡ ይገልጽበታል ።

የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ የማይፈጽምበት ፤ ከሰው ፡ ፍርድ ፡ የማያመልጥበት ፤ የእውነተኛ ፡ ብርሃት ፤ እግዚአብሔር ፡ ሳያደላ ፡ የፈጠረውን ፡ አእምሮ ፡ ሥራ ፡ ማስፈታትና ፡ ለድንቁርና ፡ መገዛት ፡ ነው ።

እናንተም ፡ በዚህ ፡ በተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ዛሬ ፡ የሰበሰብኋችሁ ፡ ልጆች ፡ ወደፊትም ፡ እተማሪ ፡ ቤቱ ፡ የምትገቡ ፡ ሁሉ ፡ የምነግራችሁ ፡ ዕውቀት ፡ ለሰው ፡ የምትጠቅም ፡ እንደሆነች ፡ በብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተጻፈ ፡ ታውቃላችሁ ። ወደፊትም ፡ የምትማሩት ፡ ነው ። ዕውቀት ፡ የተጨበጠች ፡ ማንም ፡ የማይወርሳት ፡ ገንዘብ ፡ ናት ፤ የሰማያዊንም ፡ የምድራዊንም ፡ አዋጅ ፡ የማታስፈርስ ፡ ከጥፋትም ፡

ንና ፡ ሰውቀቱን ፡ ወደ ፡ ተንኮል ፡ የሚመሬውን ፡ ነውና ፡ እውነተኛውንም ፡ ጥበብ ፡ ለሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ፳ ፡ ወርቅ ፡ የሰጠው ፡ ባሪያ ፡ ዓሥር ፡ አድርጎ ፡ በመልስ ፡ እንደተመሰገነና ፡ በብዙ ፡ አህጉር ፡ ላይ ፡ እንደተሾመ ፡ እንድቍሆኑ ፡ አንድ ፡ ወርቅ ፡ የሰጠው ፡ ባሪያ ፡ ቀብሮ ፡ አስቀምጦ ፡ ያንኑ ፡ በመልስ ፡ እንደ ረገመውና ፡ በስቃይ ፡ እንዲኖር ፡ እንደተፈረደበት ፡ እንዳትሆኑ ፡ እለምናችኋለሁ ።

አሁንም ፡ የልቦናችሁ ፡ መሠረት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ አገርን ፡ በመውደድ ፡ የተጠመደ ፡ እንዲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሁላችንን ፡ የልባችንን ፡ መሠረት ፡ በዚሁ ፡ ያድርገው ፡ ብዬ ፡ ርኅሩኅ ፡ ፈቃዱን ፡ እለምናለሁ ።

እግዚአብሔር ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታትን ፡ ይጠብቅ ።

ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ። ኢትዮጵያ ፡ ሕያው ፡ ትሁን ።

በየወሩም ፡ መጨረሻ ፡ ከሠራተኞች ፡ ደመወዝ ፡ የተቆረጠውን ፡ ገንዘብ ፡ ድምሩን ፡ ለበላይ ፡ ያስታውቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ አስተማሪዎቹና ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሥራችንን ፡ በትክክል ፡ ሠርተን ፡ ቀለባችን ፡ በማይገባ ፡ ተቆረጠብን ፡ ብለው ፡ ለበላይ ፡ ያመለክቱ ፡ እንደሆነ ፡ ዲሬክተሩ ፡ ጥፋታቸውን ፡ ገልጦ ፡ ለማስረዳት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

## ሰባተኛ ፡

የትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ለሚማሩ፡ ልጆች ፡ በየወሩ ፡ በምግብና ፡ በልብስ ፡ ረገድ ፡ የሚወጣውን ፡ ደግሞ ፡ መጽሐፍ ፡ ወረቀት ፡ ቀለም ፡ ብርዕ ፡ እርሳስ ፡ ለመግዛት ፡ የሚወጣውን ፡ ገንዘብና ፡ ተማሪዎቹ ፡ ስለትምህርታቸው ፡ የሚከፍሉትን ፡ ገንዘብ ፡ ከዋናው ፡ መዝገብ ፡ እያወጣና ፡ እያመዛዘነ ፡ ብልጫውን ፡ በየወሩ ፡ መጨረሻ ፡ ለበላይ ፡ ያስታውቃል ።

## ስምንተኛ ፡

የትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ በየሳምንቱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲገኝ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ፡ ቢተረፈ ፡ በሚያስፈልገው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ፤ ይህንኑም ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚገኝበትን ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ በማስታወቂያ ፡ ያስታውቃል ።

## ዘጠነኛ ፡

ለትምህርት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አላፊው ፡ ዲሬክተሩ ፡ ስለሆነ ፤ የትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ በትምህርት ፡ ሥራ ፡ ነገር ፡ ለመግባት ፤ ወይም ፡ አስተማሪዎቹንና ፡ ተማሪዎቹን ፡ በትምህርት ፡ ነገር ፡ ለማዘዝ ፡ አልተፈቀደም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የገንዘብ ፡ ጠባቂውን ፤ ምግብ ፡ የሚያዘጋጁትን ፤ ልብስ ፡ የሚሰፉትንና ፡ የሚያጥቡትን ፡ ዘበኞችን ፤ አትክልት ፡ ተካዮችን ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉትን ፡ ሠራተኞች ፡ ግን ፡ በተለየ ፡ የሚያዙቸው ፡ እንደራሴው ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ሥራውን ፡ ያጠፉ ፡ ቢኖር ፡ ዲሬክተሩ ፡ ለእንደራሴው ፡ እንዲያስታውቅ ፡ ይገባዋል ።

## ዓ ሥ ረ ኛ ።

የትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ በደንቡ ፡ እንደተጻፈው ፡ የቀን ፡ ተማሪ ፡ ወይም ፡ ነዋሪ ፡ ተማሪ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማስገባት ፡ ይችላል ። ተማሪዎችም ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲገቡ ፡ ከበላይ ፡ ሲፈቀድ ፡ ትእዛዙ ፡ ሁሉ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ እንደራሴ ፡ እየመጣ ፡ እንደራሴ ፡ ለትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ በጽሕፈት ፡ እያደረገ ፡ ያስታውቃል ።

## ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ።

### አሥራ ፡ አንደኛ ።

የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ ለትምህርቱ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ስለሆነ ፡ በአስተማሪዎቹና ፡ በተማሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ ስለተባለ ፡ ግን ፡ አስተማሪዎችንና ፡ ተማሪዎችን ፡ በፈቃዱ ፡ ለማግባትና ፡ ለማስወጣት ፡ አልተፈቀደለትም ። ነገር ፡ ግን ፡ አስተማሪዎች ፡ ለማብዛት ፡ ወይም ፡ ለማሳነስ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፡ በጽሕፈት ፡ እያደረገ ፡ ለእንደራሴ ፡ ያስታውቃል ። እንደራሴውም ፡ ለበላይ ፡ እያስታወቀ ፡ ከበላይ ፡ እንደተፈቀደ ፡ ያደርጋል ። ተማሪዎችንም ፡ ለማስገባት ፡ ቢሆን ፡ ከበላይ ፡ ሲፈቀድ ፡ እንደራሴ ፡ በጽሕፈት ፡ እያደረገ ፡ በላከለት ፡ ጊዜ ፡ ይቀበላል ፡ እንጂ ፡ በፈቃዱ ፡ አያስገባም ።

### አሥራ ፡ ሁለተኛ ።

የትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ ለትምህርቱ ፡ ሥራ ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ ስለተባለ ፡ ሌሎችንም ፡ አስተማሪዎችን ፡ ሁሉ ፡ በየክፍላቸውና ፡ በየሥራቸው ፡ አላፊነት ፡ አለባቸውና ፡ መጀመሪያ ፡ ዲሬክተሩ ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ በኋላ ፡ አስተማሪዎቹን ፡ ለማሳለፍ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ትእዛዙንና ፡ ሥራውን ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ሳይሰጣቸው ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ አስተማሪዎቹ ፡ አላፊነት ፡ የለባቸውም ።

### አሥራ ፡ ሦስተኛ ።

አስተማሪዎች ፡ ወይም ፡ ተማሪዎች ፡ ጥፋት ፡ ተገኝቶባቸው ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማስወጣት ፡ ያሰበ ፡ እንደሆነ ፡ አስቀድሞ ፡ ጥፋታቸውን ፡ እየጻፈ ፡ ለእንደራሴ ፡ እየሰጠ ፡ ያስወጣቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደራሴ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ በጻፈለት ፡ ደብዳቤ ፡ ጥፋታቸውን ፡ መርምሮ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመውጣት ፡ የማያበቃቸው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ነገሩን ፡ በዝርዝር ፡ በጽሕፈት ፡ አድርጎ ፡ ለበላይ ፡ ያስታውቃል ። ከበላይም ፡ የተቈረጠውን ፡ ነገር ፡ ለዲሬክተሩ ፡ ያስታውቃል ። ነገሩም ፡ ከበላይ ፡ እስኪቈረጥ ፡ በውጭ ፡ ሆነው ፡ ይቆያሉ ።

### አሥራ ፡ አራተኛ ።

የትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ ከ፩ ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ለተማሪዎች ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠትና ፡ ለማሰናበት ፡ ይችላል ። ለአስተማሪዎች ፡ ግን ፡ የበሽታ ፡ የድንገት ፡ አደጋ ፡ ካላገኛቸው ፡ በቀር ፡ የሰዓት ፡ እኩሌታም ፡ ቢሆን ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠትና ፡ ለማሰናበት ፡ አልተፈቀደለትም ።

## ሠላሳ ፡ ሁለተኛ ፡

የጤና ፡ መመስከሪያ ፡ ወረቀት ፡ አጻጻፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለው ፡ ነው ።

እኔ ፡ ሐኪም ፡ ..................................................

የልጁ ፡ ስም ፡ ..................................................

ያባቱ ፡ ስም ፡ ..................................................

ሰውነቱን ፡ መርምሬ ፡ ባለጤና ፡ መሆኑንና ፡ የሚጋባ ፡ በሽታ ፡ እንደሌለበት ፡ እመሰክራለሁ ። የፈንጣጣም ፡ በሽታ ፡ በክትባት ፡ ወይም ፡ በወረርሽኝ ፡ ወጥቶለታል ።

የሐኪሙ ፡ ፊርማ ፡

የትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደረሱ ፡ የልጁን ፡ አባትና ፡ የምስክሮቹን ፡ ፊርማ ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳው ፡ በኋላ ፡ የሚገባበትን ፡ ቀን ፡ ለአባቱ ፡ ወይም ፡ ለሞግዚቱ ፡ ያስታውቃል ።

## ሠላሳ ፡ ሦስተኛ ፡

ዕድሜያቸው ፡ ከ፲ ዓመት ፡ በታች ፡ ለሆኑ ፡ ልጆች ፡ የመኝታ ፡ ስፍራቸው ፡ ከትልልቆቹ ፡ ልጆች ፡ በላይ ፡ ይሆንላቸዋል ። በተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነዋሪ ፡ ሆነው ፡ ለሚማሩ ፡ ልጆች ፡ ጣፋጭ ፡ ምግብ ፡ እንደረሱው ፡ እየገዛ ፡ በየሳምንቱ ፡ ይሰጣቸዋል ።

## ሠላሳ ፡ አራተኛ ፡

በትምህርት ፡ ቤት ፡ ነዋሪ ፡ ሆነው ፡ የሚማሩ ፡ ልጆች ፡ ከእንደረሱው ፡ ሳያስፈቅዱ ፡መብልና ፡ መጠጥ ፡ ከውጭ ፡ እንዳያገቡ ፡ ተከልክለዋል ።

## ሠላሳ ፡ አምስተኛ ፡

በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚማሩትን ፡ ልጆች ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ወይም ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ለማየት ፡ ቢፈልጉ ፡ አስቀድመው ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ቀጥሎም ፡ ከእንደረሱው ፡ ሳያስፈቅዱ ፡ ለማየት ፡ አልተፈቀደም ። ለማየትም ፡ የሚመጡቸው ፡ ቅዳሜ ፡ ቅዳሜ ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ከአሥር ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ነው ።

## ሠላሳ ፡ ስድስተኛ ፡

በታላላቅ ፡ በዓልና ፡ በእሑድ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ፡ ትምህርት ፡ የማይማሩ ፡ ስለሆኑ ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ መጥቶ ፡ እንዲያየኝ ፡ እለምናለሁ ፡

## አርበ ፡ አንደኛ ፤

የትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስታውቅ ፡ የሒሳብ ፡ ወረቀት ፡ ወደልጁ ፡ አባት ፡ ይልካል ። የልጁም ፡ አባት ፡ ወረቀቱ ፡ ከደረሰለት ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ገንዘቡን ፡ ያልከፈለ ፡ እንደሆነ ፡ እንደራሴው ፡ ለትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ አስታውቆ ፡ ልጁን ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ያስወጣዋል ።

## አርበ ፡ ሁለተኛ ፤

በየቤታቸው ፡ እየኖሩ ፡ እየተመላለሱ ፡ ለመማር ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ ልጆች ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለሆነው ፡ ነው ። ዕድሜያቸው ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ግን ፡ ከበላይ ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ መቀበል ፡ ያስፈልገዋል ። እነዚሁም ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚችለውን ፡ ያህል ፡ ቍጥራቸው ፡ እየተወሰነ ፡ ይገባሉ ።

## አርበ ፡ ሦስተኛ ፤

እየተመላለሱ ፡ የሚማሩ ፡ ልጆች ፡ ምሳቸውን ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ለመብላት ፡ የፈለጉ ፡ እንደሆነ ፡ በየወሩ ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ብር ፡ ይከፍላሉ ፤ አከፋፈሉም ፡ በመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## አርበ ፡ አራተኛ ፤

እየተመላለሱ ፡ የሚማሩ ፡ ተማሪዎች ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ከሚዘጋበት ፡ ከትልልቅ ፡ በዓልና ፡ ከእሑድ ፡ በቀር ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዳይቀሩ ፡ ተወስኗል ። ነገር ፡ ግን ፡ በድንገት ፡ በሽታ ፤ ወይም ፡ ሌላ ፡ አደጋ ፡ ቢያገኛቸው ፡ ዕለቱን ፡ በጽሕፈት ፡ አድርገው ፡ ለዲሬክተሩ ፡ ያስታውቃሉ ።

## አርበ ፡ አምስተኛ ፤

እየተመላለሱ ፡ የሚማሩ ፡ ተማሪዎች ፡ ከየቤታቸው ፡ ከመጡት ፡ መጽሐፍና ፡ ወረቀት ፤ ቀለምና ፡ ብርዕ ፤ እርሳስ ፡ በቀር ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ማናቸውንም ፡ ቢሆን ፡ ይዘው ፡ እንዳይወጡ ፡ ተከልክለዋል ።

## አርብ ፡ ስድስተኛ ፡

በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት እየተመላለሱ ፡ የሚማሩ ፡ ልጆች ፡ ለመጽሐፍ ፤ ለቀለም ፤ ለወረቀት ፤ ለእርሳስ ፤ ለብርዕ ፡ መግዣ ፡ በየወሩ ፡ አንዳንድ ፡ ብር ፡ ይከ ፍላሉ ። ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ሁሉ ፡ በገንዘባቸው ፡ እየገዙ ፡ ያመጣሉ ።

## አርብ ፡ ሰባተኛ ።

በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነዋሪ ፡ ሆነው ፤ ወይም ፡ እየተመላለሱ ፡ የሚ ማሩ ፡ ልጆች ፡ የማይለቅ ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ ትምህርት ፡ የሚከለክል ፡ ዋና ፡ ምክ ክንያት ፡ ካላገኛቸው ፡ በቀር ፤ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተወሰነውን ፡ ትምህ ርት ፡ ሳይጨርሱ ፡ በጭራሽ ፡ ወጥቶ ፡ ለመሔድ ፡ አልተፈቀደላቸውም ። አለፈቃድም ፡ ቢወጡ ፡ ተመልሰው ፡ እንዳይገቡ ፡ ይከለከላሉ ፤ በመጀመሪያም ፡ የከፈሉትን ፡ ገን ዘብ ፡ መልሱልን ፡ ለማለት ፡ አይችሉም ።

## አርብ ፡ ስምንተኛ ።

በተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነዋሪዎች ፤ ወይም ፡ ተመላላሾች ፡ ልጆች ፡ የሚከፍሉት ፡ ገንዘብ ፡ ለጊዜው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ ስለተ ወሰነ ፤ ወደፊት ፡ የገንዘብ ፡ መርከስና ፡ መወደድ ፡ እየታየ ፡ ለመጨመርም ፡ ለማ ጉደልም ፡ ይቻላል ።

## በምግብ ፡ ቤት ፡ ለየአንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ዕቃ ።

## አርብ ፡ ዘጠነኛ ።

ሁለት ፡ የወጥ ፡ ሣህን ፤
አንድ ፡ የሾርባ ፡ ሣህን ፤
አንድ ፡ የሾርባ ፡ ማቅረቢያ ፡ ሣህን ፡ ለ፰ ፡ ተማሪዎች ፤
ሦስት ፡ የምግብ ፡ ማቅረቢያ ፡ ሣህን ፡ ለ፰ ፡ ተማሪዎች ፤
አንድ ፡ በአንድነት ፡ የሆነ ፡ የዘይት ፤ የጨው ፤ የቁንዶ ፡ በርበሬ ፡ ለ፰ ፡ ተማሪዎች ፤

አንድ ፡ ማብረጃ ፡ የወሀ ፡ ለ፬ ፡ ተማሪዎች ፤

አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ለየአንዳንዱ ፤

አንድ ፡ ቢላዋ ፤

አንድ ፡ ሹካ ፤

አንድ ፡ የሸርባ ፡ ማንካ ፤

አንድ ፡ የቡን ፡ ማንካ ፤

አንድ ፡ የቡን ፡ ሲኒ ፤

አንድ ፡ የሻይ ፡ ሲኒ ፤

አንድ ፡ የገበታ ፡ ላይ ፡ ፎጣ ፡ በመብል ፡ ጊዜ ፡ ለየአንዳንዱ ፤

አንድ ፡ የስኳር ፡ ማቅረቢያ ፡ ለ፰ ፡ ተማሪዎች ።

<u>በመኝታ ፡ ቤት ፡ ለየአንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ዕቃ ።</u>

<u>ሃምሳኛ ።</u>

አንድ ፡ አልጋ ፤

አንድ ፡ ፍራሽ ፤

ሁለት ፡ ያልጋ ፤ ምንጣፍ ፤

አንድ ፡ ትራስ ፤

ሁለት ፡ የትራስ ፡ ልብስ ፤

ሁለት ፡ የብርድ ፡ ልብስ ፤

ሁለት ፡ የሌሊት ፡ ቀሚስና ፡ ሱሪ ፤

አንድ ፡ ትንሽ ፡ ጠረጴዛ ፡ (በውስጡ ፡ የሽንት ፡ ቆፍ ፡ የሚያስቀምጥ ፤)

አንድ ፡ ማብረጃ ፡ ለውሀ ፤

አንድ ፡ ብርጭቆ ፤

ሁለት ፡ የመታጠቢያ ፡ ፎጣ ፤

አንድ ፡ ብሩሽ ፤

አንድ ፡ ሚዶ ፤

አንድ ፡ የጥርስ ፡ ብሩሽ ፤

አንድ ፡ ሰፍነግ ፡ ለመታጠቢያ ፤

አንድ ፡ የጥርስ ፡ መታጠቢያ ፡ ዱቄት ፤

አንድ ፡ ሳጥን ፡ የተማሪው ፡ ስምና ፡ ንምራ ፡ የተጻፈበት ፡ ለየአ
ንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ የሚያስፈልግ ፡ የዘወትር ፡ ልብስ ፤

## ሃምሳ ፡ አንደኛ ፡

አንድ ፡ ከኪ ፡ ኰት ፡
አንድ ፡ ከኪ ፡ ቁምጣ ፡ ሱሪ
ሁለት ፡ የውስጥ ፡ ቀሚስ ፡
ሁለት ፡ የገላ ፡ የውስጥ ፡ ሹራብ ፡ የጥጥ ፡
ሁለት ፡ መሐረም ፡
አንድ ፡ ቆብ ፤ ቁጥርና ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ምልክት ፡ ያለበ
አንድ ፡ የጠዋት ፡ ልብስ ፤ ወይም ፡ በርኖስ ፡
አንድ ፡ ነጠላ ፡ ጫማ ፡

## የበዓል ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ መገናኛ ፡ ልብስ ፡

አንድ ፡ ኮት ፡
አንድ ፡ ሱሪ ፡
ሁለት ፡ የገላ ፡ የውስጥ ፡ ሹራብ ፡ የጥጥ ፡
ሁለት ፡ መሐረም ፡
አንድ ፡ የአውሮፓ ፡ ጫማ ፡

ለያንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ ለትምህር ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሣሪያ ፡

## መጽሐፍ ፡ በያይነቱ ፡

## ሃምሳ ፡ ሁለተኛ ፡

አንድ ፡ ደብተር ፡
አንድ ፡ ብርዕ ፡
አንድ ፡ መድ ፡ ቀለም ፡
አንድ ፡ እርሳስ ፡
አንድ ፡ ላፒስ ፡
አንድ ፡ የርሳስ ፡ ማሾያ ፡ በአንድ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ
አንድ ፡ ሰንጢ ፡ በአንድ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡

## ሃምሳ ፡ ሶስተኛ ፡

እኔ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ በቆ
ሁት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ደን
እየተሠራ ፡ ቆይቶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየታየ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ይ
ደሳል ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ. ም. አዲስ ፡ አበባ ።

